# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## <u>ዜና ዘገባ</u>

**ግንቦት 28 ቀን 2003 ዓ.ም**

**የሞት ፍርድ ተወስኖባቸው የነበሩት የደርግ ባለስልጣናት በምህረት እድሜ ልክ ሆነላቸው፤**

**በቅርቡ ከእስር ይፈታሉ ተብሎ ይጠበቃል፤**

**በእቃዎች ላይ ተጥሎ የነበረው የዋጋ ተመን በነጋዴው ትግል ተነሳ፤**

**የኢንጅነር ኃይሉ ሻውል በፌዴራል ፖሊስ መታፈን እያነጋገረ ይገኛል፤**

እጃቸው በሰው ልጆች ደም የጨቀየው የደርግ ባለስልጣናት ከሞት ፍርድ ወደ እድሜ ልክ እስራት እንደተቀየረላቸው ታወቀ፡፡በሰው ልጆች ላይ አሰቃቂ ግፍ እና ስቃይ ለ17 ዓመታት ሲያደርሱ የነበሩት እነ ለገሰ አስፋው በወንጀለኛው ወያኔ ቡድን የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው ግዜያቸውን ሲጠባበቁ ባለበት በዚህ ግዜ የሞት ፍርዱ ወደ እድሜ ልክ እንዲቀየርላቸው መደረጉ ለቀጣይ ማስፈታቱ ሂደት ለማመቻቸት እንዲረዳ መሆኑም ታውቆዋል፡፡

በወያኔው ፕሬዝዳንት እድሜ ጠገቡ መቶ አለቃ ግርማ ወ/ጊዮርጊስ ፊርማ ጸድቆ እስራቱ የተሻሻለላቸው የደርግ ባለስልጣናት 23 ሲሆኑ ከነዚህ መሀከልም ለገሰ አስፋው፤ ፍቅረ ስላሴ ወግደረስ፤ ፍስሀ ደስታ ፤መላኩ ተፈራ እና ደበላ ዲንሳ እንደሚገኙበት ወያኔ ባወጣው መግለጫ አስታውቆዋል፡፡

ህዝብ በወያኔ አልሞ ተኳዋሽ ቅልብ ወታደሮች እየተዘነጠሉ በየአደባባዩ ሲገደሉ ትንፍሽ ያላሉት የእምነት አባት ነን ባዮቹ እነ አባ ገብረመድህን ዛሬ የወያኔ ቡድን የደረሰበትን የፖለቲካ ኪሳራ ለመጠገን ሲሉ የደርግ ባለስልጣናትን ለማስፈታት ከላይ ታች ሲሉ የከረሙ መሆኑ የታወቀ ሲሆን ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ ሰሞኑን የሞት ፍርዳቸውን ወደ እድሜ ልክ ፍርድ ማውረዱን አስታውቀዋል::

ለ17 ዓመታት ህዝብን እንደ ሳር ሲያጨዱና ሲከምሩ አልፎ ተርፎ ሲያጋዩ እንዲያም ሲሉ በአንድ ጉድጉዋድ በመቶዎች የሚቆጠሩ ዜጎችን ሲቀብሩ የነበሩት ሰው በላው የደርግ ባለስልጣናት ለ20 ዓመታት በእስር ላይ የቆዩ ሲሆን በእምነት አባቶች በኩል ከእስር እንዲፈቱ ከፍተኛ ስራ ሲሰራ ቢቆይም በወቅቱ ግፍ የተፈጸመባቸው ቤተሰቦችና የሰማዕታቱ ቤተሰቦች ባቀረቡት ተቃውሞ መሀል ላይ ጋብ ብሎ የነበረ ቢሆንም ሰሞኑን ቀደሞ የተጀመረውን ለማስቀጠል ይረዳ ዘንድ  የእስራት ቅጣታቸው እንዲሻሻል መደረጉም ታውቆዋል::

የወያኔ ፖለቲካ በየግዜው ወደ ቁልቁል እየተምዘገዘገ በመውረድ ላይ በመሆኑ ይሄንን ውድቀት ለማዳን ሲባል ብቻ በህዝብና በሀገር ላይ ግፍ እና በደል ለፈፀሙት ደርጎች ይቅርታ በማድረግ የህዝብ ድጋፍ ለማግኘት እየጣረ ቢሆንም በገዛ አባሎቹ በተለይ የህወሀት ከፍተኛ ባለስልጣናት አሁንም ቅሬታ እንዳላቸው ተገልፆዋል::

ወያኔ ሀገሪቱን ለባዕዳን ቆራርሶ እያደለ ህዝቡዋን ለድህነት ዳርጎ ባለበት እና ከፍተኛ የፖለቲካ ድቀት በደረሰበት በዚህ ግዜ አንዴ የህዳሴውን ግድብ እሰራለሁ ሌላ ግዜ ልማት አፋጥናለሁ እያለ ያልተሳካለት በመሆኑ አሁን ደግሞ የደርግ ባለስልናትን ከእስር ፈትቶ ብሔራዊ እርቅ አወረድኩ በሚል ህዝብን ሊሸነግልና ሊያታልል መሆኑን  የተጎጂ ቤተሰቦች እየተቃወሙ ይገኛሉ::

ብሔራዊ እርቅ ተብሎ የደርግ ባለስልጣናት ከእስር የሚፈቱ ከሆነ በውጭ ያሉ በወያኔ ላይ ቅሬታ ያላቸው ዜጎች ......በሀገር ውስጥ ደግሞ በአመለካከታቸው ብቻ እየታፈሱ በየእስር ቤቱ ታጉረው ያሉት ዜጎች ተፈትተው ሁሉም ይቅር ለእግዜአብሔር ተብሎ መፈጸም አለበት እንጂ የወያኔን ስልጣን እድሜ ለማረዘም ሲባል ብቻ የደርግ ባለስልጣናትን ፈትቶ እርቅ አወረድኩ ማለቱ የቀልዶች ሁሉ ቀልድ ነው ያሉት የሰማዕታቱ ቤተሰቦች ዛሬ ወያኔ በሀገር እና በህዝብ ላይ እየፈጸመ የሚገኘውም ከደርግ የበለጠ በመሆኑ ይሄንንም ለመሸፋፈን እንዲረዳው መሆኑንም እነዚሁ የተጎጂ ቤተሰቦች ይገልጻሉ::

የእምነት አባቶቹ ቀድሞ ከጀመሩት የማስፈታት ሂደት በተጨማሪ ይቅርታው የተሙዋላ እንዲሆን ይፈቱ ብለው ለፕሬዝዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ ያቀረቡ ሲሆን አሁን ደግሞ ህብረተሰቡ ይቅር እንዲል በሚል በሚዲያ ቀርበው ጥሪ እያቀረቡ ሲሆን ምናልባትም በሚቀጥለው ሳምንት ውስጥ የደርግ ባለስልጣናቱ ከእስር ሊፈቱ እንደሚችሉ ከወዲሁ እየተነገረ ይገኛል::

ወያኔ ነጋዴውን አሽመደምድበታለሁ..... የህዝብ ድጋፍ ደግሞ አገኝበታለሁ ብሎ ጥናት ሳይደረግበት በግብታዊነት የወሰደው እርምጃ ለከፍተኛ ኪሳራና ውርደት የዳረገው መሆኑ ታወቀ::

ከአምስት  ወራት በፊት የውስጥ ፖለቲካው ተወጥሮ ሊፈነዳ በተቃረበበት እና በኑሮ ውድነት ሳቢያ   በሰሜን አፍሪካና በዓረብ ሀገራት የተጀመረው የህዝብ ተቃውሞ ስላስደነገጠው ነጋዴውን ለማስፈራራት ብሎም የህዝቡን አቅጣጫ ለማስቀየር በሚል ድንገት ሳይታሰብ በተወሰኑ የፍጆታ እቃዎች ላይ የዋጋ ተመን ማውጣቱን ተከትሎ ከፍተኛ ውግዘት ከህዝቡም ሆነ ከነጋዴው ሲደርስበት የነበረ ሲሆን ይህንኑ ተከትሎ  ሰሞኑን  የዋጋ ተመኑን ለማንሳት መገደዱ ታውቆዋል::

ለህዝብ የማይጠቅም ከህዝብ ፍላጎት   ውጭ የውስጥና የውጭ ፖለቲካውን ለማርገብና ለማስተንፈስ ሲል ብቻ እየወሰዳቸው ያሉት እርምጃዎች መልሶ ለውድቀት እና ለኪሳራ እየዳረጉት ያለው የወያኔ ቡድን ሰሞኑንም በነጋዴው ቆራጥ እርምጃ የጣለባቸውን  የዋጋ ተመኖች ሳይወድ በግድ እንዲያነሳ መገደዱን በይፋ ገልፆዋል::

በቂ ጥናት ሳይደረግበት...... ሙያተኞች ሳይመክሩበት..... በግብታዊነት የራሱን ችግር ለቀርፍበት እና ጊዜያዊ ፋታ  ለማግኘት ሲል ብቻ በጥቂት የፍጆታ እቃዎች ላይ አውጥቶ የነበረውን የዋጋ ተመን እንዲያነሳ  በተደጋጋሚ ግዜ ጥያቄ ሲያቀርቡ የነበሩት ነጋዴዎች በወሰዱት የተባበረ እርምጃ ሳይወድ በግዱ የጣለውን ተመን ለማስነሳት እንደቻሉ ገልፀዋል::

በሀገር ውስጥ የሚመረተውና በውድ ዋጋ እየተሸጠ ያለው ስኩዋር ሳይቀር ከፋብሪካ በ3 ብር ከ50 ሳንቲም አውጥቶ ለህዝቡ በ14 ብር እየሸጠ የሚገኘው ይሄው  የወያኔ ቡድን ነጋዴውን በመፍራት እና በመጥላት አቅሙን አዳክሞ ጥገኛ ለማድረግ አስቦ የወሰደው እርምጃ ቢሆንም ያልተሳካለት ከመሆኑም በላይ ከእንግዲህ ነጋዴውን  ሊቆጣጠረው እንደማይችል አስረግጦ ያሳየ መሆኑንም ነጋዴዎች እየገለፁ ናቸው::

ከዚህ በፊት ህዝቡ እና ነጋዴዎች በመግባባት እና በመተሳሰብ ሲገበያዩ የነበረውን ሂደት መሀከል ደንቃራ ገብቶ ለመከፋፈል ጥረት ቢያደርግም ያልተሳካለት የወያኔ ቡድን በቅርቡ የዋጋ ተመን አወጣሁ ባለው ላይ እንደገና እንዲያነሳ በመገደዱ  ለከፍተኛ የፖለቲካ ኪሳራ የተዳረገ መሆኑ ተረጋግጦዋል::

ለአምስት ወራት ያህል ግዜ ብቻ የቆየው የዋጋ ተመኑ ለህዝቡ አንዳችም ጠቀሜታ ያልሰጠ ከመሆኑም በላይ እቃዎቹ ከገበያ እንዲጠፉ አስተዋፅኦ ያደረገ ሲሆን የገበያ ስርዓቱን ጭምር ያበላሸ መሆኑም ታውቆዋል::

የዋጋ ተመኑ ከመውጣቱ በፊት 7ብር ሲሸጥ የነበረው የሳሙና ዋጋ ሰሞኑን እንደፈለጋችሁ መሸጥ ትችላላችሁ ተብሎ በነፃ በተለቀቀው መሰረት ወደ 9 ብር ያሻቀበ ሲሆን የአንድ ኪሎ ስጋ ዋጋ ከዋጋ ተመኑ በፊት 70 ብር የነበረ ሲሆን አሁን ግን ከ90 ብር እስከ 100 ብር እየተሸጠ እንደሚገኝም ለማወቅ ተችሎዋል::

ወትሮም ለህዝብና ለሀገር የማያስበው የወያኔ ቡድን ህዝቡን ሳያማክርና ባለሙያዎችን ሳያሳትፍ የራሱን የፖለቲካ ችግር ለማስተንፈስ ብሎም ለማርገብ ብቻ  በወሰደው እርምጃ ነጋዴውም ሆነ ህዝቡ ለከፍተኛ ኪሳራና እንግልት ተዳርጎ የነበረ ሲሆን ከሁሉም በላይ ግን የወያኔ ፖለቲካ ከመዋረዱም በላይ የዘቀጠበት ሁኔታ መፈጠሩን ነጋዴዎቹ ሲናገሩ ተደምጠዋል::

በጥቂት እቃዎች ላይ ያለ በቂ ጥናት ያስቀመጠውን የዋጋ ተመን ሳይወድ በግድ በነጋዴው አስገዳጅነት እንዲነሳ ከተደረገበት ዕለት ጀምሮ የእቃዎች አቅርቦት በገፍ የሚገኙ ቢሆኑም የዋጋቸው ጉዳይ ግን የሚቀመስ እንዳልሆነ ህዝቡ እየገለፀ ይገኛል፡፡

ረቡዕ ግንቦት 24 ቀን 2003 ዓ.ም የዋጋ ተመኑ ከመነሳቱ ከሁለት ቀናት በፊት ጀምሮ ነጋዴዎች የዋጋ ተመኑን ሰርዘው በራሳቸው ባወጡት ተመን እየሸጡ እንደነበር ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን ጠቅሶ የዋጋ ተመኑ በይፋ ከወጣበት ዕለት ጀምሮም ዋጋው እጅግ በሚያስገርም ሁኔታ ከመቼውም ግዜ በላይ ማሻቀቡን ገልፆዋል፡፡

የወያኔ ቡድን የዋጋ ተመን ብሎ ያወጣው መመሪያ ነጋዴውን ከህዝቡ ለመነጠል እና ለማናከስ የወሰደው እስትራቴጂ ነበር ያሉት ነጋዴዎቹ ህዝቡ ምስጢሩን በማወቁና በመረዳቱ የታሰበው እቅድ ግቡን ሳይመታለት የቀረ ሲሆን ነጋዴውም መሀከል ገብቶ አባል የሆኑና ያልሆኑ በሚል ለመከፋፈል ጥረት ቢያደርግም ሳይሳካለት ከመቅረቱም ባሻገር ለከፍተኛ ውርደት እና ኪሳራ የተዳረገበት መሆኑን ጨምረው ገልፀዋል፡፡

የገበያውን ሁኔታ በአንዳንድ ቦታዎች ተዘዋውሮ የተመለከተው ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን እንዳለው ከሆነ ጠፍተው የነበሩት እቃዎች በሚገርም ሁኔታ ተደርድረው የገቡ ሲሆን ዋጋቸው ከአንዱ ሱቅ አንዱ የተለያየ መሆኑን ጠቅሶ ይሁን እንጂ ከህዝቡ የመግዛት አቅም በላይ የሆኑ እቃዎች እንዳሉም አስረድቶዋል፡፡

የወያኔ ቡድን ነጋዴውን ረግጦና አሽከርክሮ ለመግዛት ዋነኛ እቅዱ ነበር ያሉት የንግዱ ህብረተሰብ በመሀከላችን ጥቂት ሰርጎ ገቦችን አሰማርቶ ሊከፋፍለን ሞክሮ የነበረ ቢሆንም በእኛ ጥንካሬ ያሰበውን ልናከሽፍበት ችለናል ብለዋል፡፡

አክለውም በቅርብ ግዜ ጀምሮ የወያኔ ደጋፊ ነጋዴዎች ማህበር የሚል ልክ እንደ ሴቶችና ወጣቶች ፎረም ማህበር አይነት በነጋዴዎችም ላይ የወያኔ ተለጣፊዎችን ቢያቋቁምም ነጋዴው ለወያኔ ካለው ጥላቻ የተነሳ ዞር ብሎ ያላየው በመሆኑ መልሶ ከበረሀ የመጡና ከፍተኛ መንቀሳቀሻ ካፒታል የተመደበላቸውን አባሎቹን ለማሰባሰብ ብቻ ተገድዶዋል ሲሉም ገልፀዋል፡፡

ዛሬ አንቱ የተባሉ ነባር ነጋዴዎችን በሚሰሩት ስራ ላይ ጫና በመፍጠር እና በማስፈራራት አልፎ ተርፎ በቫት እና በተለያዩ ሰበቦች እየለቀሙ ለእስር እየዳረጉዋቸው የሚገኙ ሲሆን እስከ አሁን ከ10 በላይ የሚሆኑ ታዋቂ ነጋዴዎችና ኢንቨስተሮች አዲግራት እና መቀሌ እስር ቤቶች ውስጥ ታጉረው እየተሰቃዩ ቤተሰቦቻቸውም እንዳያዩዋቸው ተደርጎ እንደሚገኙ ለንግዱ ህብረተሰብ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ይገልፃሉ፡፡

አንዳንዶቹንም በባንክ ያላቸውን ገንዘብ እንዳያንቀሳቅሱ ተከልክለው ወደ ውጭ ሀገር ጭምር እንዳይወጡ ሁሉ ተደርጎ ለቁም እስረኛነት የተዳረጉ ከመሆኑም በተጨማሪ እንቅስቃሴያቸው በሙሉ በደህንነት ልዩ ክትትል ስር ሊወድቅ እንደቻለም እነዚሁ ወገኖች አጋልጠዋል፡፡

በተለይ ለወያኔ የስልጣን እድሜ ማራዘሚያ የነበሩትና በቸገረው ግዜ ሁሉ አለን ከጎንህ ነን የሚሉት ባለሀብቶች ዛሬ ከወያኔ ጋር ሆድና ጀርባ በመሆናቸው ገሚሱን ለእስር ሌሎቹን ለቁም እስር ዳርጎዋቸው በአይነ ቁራኛ እንዲጠበቁ ማድረጉ ወያኔ ከበረሀ ይዞት የመጣው የድመት ባህሪው መሆኑን የሚያረገግጥ ነው ሲሉም እነዚሁ ለንግዱ ህብረተሰብ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ይገልፃሉ::

በሌላ ዜና የወያኔን ፖለቲካ ካደመቁት እና የስልጣን እድሜ አራዘሙ ከተባሉት መሀከል አንዱ የሆኑት የመኢአድ ሊቀመንበር ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ሰሞኑን ከንግድ ቢሮዋቸው በፌዴራል ፖሊስ ተይዘው መወሰዳቸውን የአይን እማኞች ገለፁ::

ግንቦት 16 ቀን 2003 ዓ.ም ብስራተ ገብርኤል ተብሎ በሚጠራው ሰፈር ባሰሩት ግዙፍ የንግድ ተቋዋም ባለው ቢሮዋቸው ውስጥ ባሉበት ወቅት ከ30 በላይ የፌዴራል ፖሊስ ታጅበው ወደ ፌዴራል ፖሊስ ተወስደው ለሶስት ሰዓት ያህል ታስረው እንደተፈቱ ታውቋዋል::

የምርጫው ሂደት ትክክል ነው ብለው የምርጫ ስነ ምግባር ደንቡን ተሽቀዳድመው የፈረሙት የመኢአድ ሊቀመንበር ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ህዝቡን ለአመፅ እየቀሰቀሱ ነው በሚል በፌዴራል ፖሊስ ተይዘው ሲወሰዱ የተመለከቱ የአይን እማኞች አንድን ግለሰብ በስልክ ደውሎ መጥራት ሲቻል ከ30 በላይ የፌዴራል ፖሊስን አንጋግቶ ሌላውን ህብረተሰብ መረበሽ እና ማሸበር ተገቢ አይደለም ያሉት የአካባቢው ነዋሪዎች ወያኔ ፍርሀት ውስጥ መውደቁን የሚያሳዩ ምልክቶች ናቸው ሲሉም ገልፀዋል::

የፌዴራል ፖሊስ ምክትል አዛዥ ሀሰን ሺፋ ለሶስት ሰዓት ያህል በአንድ ቢሮ ውስጥ አግቶ ያቆያቸው ከመሆኑም በላይ ህዝቡን ለመቀስቀስ ውስጥ ውስጡን እየሰራችሁ ነው ስለዚህ ከእንግዲህ በተመሳሳይ ሁኔታ ቢሞክሩ እርምጃ እንደሚወስደባቸውም አምርሮ የገለፀላቸው መሆኑም ታውቋዋል::ከዚህ ቀደም የምኒልክ ጋዜጣ አዘጋጅ የነበረው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ በተመሳሳይ ከመንገድ ላይ በደህንነቶች ተጠልፎ ሀሰን ሽፋ ቢሮ ቀርቦ የነበረ ሲሆን በወቅቱም የምታቀርባቸው አመጽ ቀስቃሽ ፅሁፎችህን ካላቆምክ ከእንግዲህ አናስርህም እንደፋሀለን ብሎት እንዳባረረው መግለፁ አይዘነጋም::

በአሁኑ ሰዓት ዜጎች ከምንግዜውም በላይ ከየጎዳናው ላይ እየታፈሱ ለእስር እየተዳረጉ ያሉበት ወቅት ቢሆንም አንድም የሀገር ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲ ደፍሮ ለመቃወምና ሰላማዊ ሰልፍ ለመጥራት ያለመቻሉ ለወያኔ የልብ ልብ የሰጠው መሆኑንም የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ይናገራሉ::

በተንጣለለው ሜዳ ላይ የተለያዩ የመዝናኛ ማዕከሎች የተገነባው የኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ንብረት የሆነው ላፍቶ የሚል ስያሜ የተሰጠው የንግድ ተቋዋም ምርጫ 1997 ዓ.ም ህዝቡ ነፃነቷን ብሎ እየተዋደቀ ባለበት ግዜ እሳቸው ይህንን የንግድ ተቋዋም እያስገነቡ እንደነበር ያጋለጡት ቅርበት ያላቸው ወገኖች ይሄ ብቻ ሳያንሳቸው ምርጫ 2002 ላይ የወያኔን ድራማና ድግስ ለማድመቅ ተሽቀዳድመው የምርጫ ስነ ምግባር ደንቡን በመፈረማቸው ህዝቡ ድጋፉን የነፈጋቸው በመሆኑና ወያኔም እሳቸውንና መሰሎቻቸውን ማጣት ስለሌበት በአሁኑ ወቅትም የህዝብ ድጋፍ እንዲያገኙ ሆን ተብሎ የተወሰደ እርምጃና የተሰራ ስራ ሊሆን ይችላል ሲሉም እነዚሁ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ይገልፃሉ::

በአሁኑ ሰዓት በመጠኑም ቢሆን ወያኔን የሚያስደነግጠውና የሚያስበረግገው መድረክ የተሰኘ ው የብዙ ፓርቲዎች ስብስብ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ላይ የሚገኝ ሲሆን ከነዚህም መሀከል ሹም ሽረት እያደረገ እንደሚገኝ አስታውቆዋል።

በተለይ የመድረክ ዋነኛ አውታር ነው የሚባልለት አንድነት ፓርቲ የወያኔ 20ኛ ዓመት በተከበረበት ዕለት ግንቦት 20 ቀን 2003 ዓ.ም ጠቅላላ ጉባኤ በቢሮው ውስጥ አድርጎ በወ/ት ብርቱካን ምትክ ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳን ፕሬዝዳንት አድርጎ የሾመ ሲሆን በህዝብ ግንኙነቱ በአቶ ስዬ አብርሀ ምትክ ደግሞ አቶ አንዱአለም አራጌን መሾሙን ባወጣው መግለጫ አስታውቆዋል።

የመድረክ አባል የሆነው አንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር ሆና ለረዥም ግዜ የቆየችው ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ከእስር ከወጣች በሁዋላ ወደ ፖለቲካው ሳትመለስ ለትምህርት በሚል ወደ አሜሪካ በማቅናትዋ በምትኩዋ ሌላ ፕሬዝዳንት መምረጥ በማስፈለጉ ዶክተር ነጋሶን መተካት ግድ ብሎዋል ያለው ፓርቲው በተመሳሳይ ስዬ አብርሀም የትምህርት እድል አግኝቻለሁ ብሎ ወደዚያው በማቅናቱ በምትኩ አንዱአለም አራጌን ማስቀመጡን ገልፆዋል።

አንድነት ፓርቲ ብርሀን ለአንድነት እና ለዲሞክራሲ ከተሰኘ ፓርቲ ጋር ውህደት ለመፍጠር የረዥም ግዜ ፕሮግራም ይዞ የነበረ ቢሆንም ይሄንኑ እውን ለማድረግ ሆቲል ኪራይ ፈጽሞ የነበረ ቢሆንም በወያኔ የደህንነት ክፍል በመከልከሉ ውህደቱ ሊሳካ ያልቻለ መሆኑን የገለፀው ፓርቲው በቅርቡ ግን የውህደቱ ፕሮግራም በቢሮ ውስጥ እንደሚፈጸም ገልፆዋል።

የሆቲል ኪራይ ጭምር ተከፍሎ የነበረውን የወያኔ ቡድን በተለይ የአንድነት ፓርቲን በመፍራቱ ብቻ ስብሰባውን ሊያደናቅፈው ችሎዋል ያለው ፓርቲው ተወደደም ተጠላ አሁንም እንዋህዳለን ሲል በበተነው መግለጫ አስታውቆዋል። መድረክ የተሰኘው ፓርቲም ወያኔን ቆርጦ ለመታገል እየገለፀ ሲሆን ለዚህም እንዲረዳው ሙሉ ለሙሉ በቅርቡ ወደ ግንባርነት እንደሚለወጥ በይፋ አውጆዋል።